# <u>ክፍለ ትምህርት አምስት</u>

## *መሪዎች መልዕክት ያስተላልፋሉ።*

*በአራተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ የዳዊትን ምሳሌነት በመከተል ያገኘናቸውን የመሪነት መመሪያዎችን እንዴት በሥራ ላይ ለመተርጎምም እንደምንችልና ድርጅት በሚለው ሃሳብ ላይ በማተኮር የድርጅት ዓይነቶችንና መመሪያዎችን ተመልከተናል።*

*በዚህ በአምስተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ የኢያሱን የመሪነት መመሪያዎች እንደ ምሳሌ በመውሰድ በሥራ በመተርጎም የሚያስፈልገውን ጥረት በማድረግ በመሪነት ሥራ ላይ ላለ ሰው ከሌሎች ጋር ግንኙነት እያደረገ ወቅታዊ መልእክቶችን ማስተላለፍ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንመለከታለን።*

*የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል*

- *የኢያሱ ምሳሌት*
- *መልእክትን የማስተላለፍ ሂደት*
- *መሪዎች አለመግባባቶችን ያስወግዳሉ*

---------------------------------------------

***የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች***

*ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ።*

- *የኢያሱን ሕይወት አስመልክቶ የአመራር አሠራሮችን በመከተል እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርጋቸውም መግለጽ።*
- *ግንኙነትና መልእክት ማስተላለፍ የሚለውን ሃሳብ መግለጽ። መሪነትን በተመለከተ የመልእክትን በትክክል ማስተላለፍ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መግለጽ።*
- *ውጤታማ መሪ ለመሆን ሰዎች የሚሰጡትን አስተያየት ማዳመጥና ምላሽ መስጠት አስፈላጊነቱን ለመግለጽ።*

----------------------------------------------------------

***የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች***

1/ *መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ* 1፣3፣1-13፣ 4፡1-8፡ 6፡6-17፡ 18፡፣21 43-45 *እና ምዕራፍ* 22 *አንብብ።*

2/ የክፍለ ትምህርቱን ማጠናከሪያ እንደሚገባ አጥና። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን መልስ።

3/ በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር መልሶችህን በማስተያየት የተሳሳትከው ካለ አስተካክል።

**የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ**

**የኢያሱ ምሳሌነት**

**ዓላማ 1 መጽሐፈ ኢያሱን መሠረት በማድረግ መልእክቱን ለሰዎች ለማስተላለፍ ምሳሌነቱንና፣ የተጠቀሱትን ሰባት ዓይነት መልእክትን የማስተላለፊያ ዘዴዎችን ለመግለጽ**

ከኢያሱ ሕይወትና ሥራ ለአንድ መሪ የሚያስፈልጉትን አብዛኛዎቹን ባሕርያት ለመቅሰም ይቻላል። ተከታይ መሆንን፣ በኋላም ደግሞ መሪ መሆንንና ሌሎችን ማበረታታትን የተማረው ከሙሴ ነበር። ከሰዎች ጋር አብሮ ለመጋራት አንዳንድ ችግሮች ገጥመውታል። የጌታን ምሪት ባለመሻቱም አንዳንድ ስህተቶችን ፈጽሟል። በጥንቃቄ አቅዶችን አውጥቷል። ድፍረት ለተሞላበት ሥፍራ ምሳሌ ሆኗል። በሰላዮቹና በረዓብ ሲያደርግ እንደተመለከትነውም የሚፈልገውን ዓላማ ግብ ላይ ለማድረስ በሌሎች አማካይነት ሰርቷል።

ኢያሱ የዓይነተኛ መሪና በሌሎች ሁኔታዎችም ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ሰው ለመሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለንም። ይሁን እንጂ በዚህ ትምህርት አንዱን በጣም አስፈላጊ የሆነውን የኢያሱን ሕይወት ገጽታ ብቻ ነው የምንመለከተው። በተዋጣለት ሁኔታ መልእክትን ለሰዎች ማስተላለፍን በሚገባ የተረዳ መሪ በመሆኑ እንደሚገባ ተግባር ላይ በማዋል ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር እንዴት እንደሚገናኝ የሚያውቅ መሪ መሆኑ ተመስክሮለታል።

አንድ መሪ ሃሳቡን ወይም መልእክቱን እንደሚገባ ለሌሎች ማስተላለፍ ሳይችል ሲቀር የሚፈጠር ችግር ይኖራል። ምንም እንኳ ሰዎቹ ብቁዎች ቢሆኑም ሥራ ሲበዛባቸውና መልእክትን በትክክል ማስተላለፍ ሳይችሉ ሲቀሩ ጌታን በቅንነት ለማገልገል የሚፈልጉ ቢሆኑም በቀላሉ አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል።

በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል አልፎ አልፎ አለመግባባት ሊፈጠር እንደሚችል ከመጽሐፈ ኢያሱ የምንመለከተው አንድ ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ታሪክ አለ። የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገዶች እኩሌታ ከዮርዳናስ ወንዝ በስተምሥራቅ የርስት ድርሻቸውን ተቀብለው እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ ርስታቸውን መውረስ ከነበረባቸው ሌሎች እስራኤላውያን ጋር አብረው ሄዱ። ውጊያው በድል ከተጠናቀቀ በኋላ ኢያሱ ባረካቸውና ወደ ርስታቸው ተመለሱ (ኢያሱ 22)።

በከነዓን ምድር ወዳለው ወደ ዮርዳኖስ አቅራቢያም በመጡ ጊዜ የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች የምናሴም ነገድ እኩሌታ በዚያ በዮርዳኖስ አጠገብ ታላቅ መሰዊያ ሠሩ። ይህም ሌሎች ነገዶችን በጣም ስላስቆጣቸው ሊወጓቸው ተነሡ። የእግዚአብሔር መሰዊያ መኖር ያለበት በሴሎ ብቻ እንደሆነ ከዚያ በፊት ስምምነት ተደርጎ ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት የእውነተኛው አምላክን አምልኮ ከሌሎች አሕዛብ አምልኮ መሠዊያ ለመለየት ነበር። ስለዚህም ወንድሞቻቸው ከእምነት እንዳፈነገጡና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዳፈረሱ አሰቡ።

የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ተደናግጠው "**በዚህ ሥፍራ መሥዋዕት የማቅረብ ዓላማ የለንም። በፍጹም አልተረዳችሁንም። እኛ ሁላችን በሴሎ እውነተኛውን አምላክ የሚያመልኩ ወገኖቻችን አካል መሆናችንን ሁሉም እንዲያውቅልን እንፈልጋለን፣፡ እግዚአብሔርን ማክበር እንጂ በእርሱ ላይ የማመጽ ዓላማ የለንም። ዋናው ዓላማችን የሚቀጥለው ትውልድና እኛም የእርሱ ሕዝብ መሆናችንን እንዲያውቁ መታሰቢያ እንዲሆን ብቻ ነው ይህን መሠዊያ የሠራነው**" አሏቸው።

ከቅርብ ጊዜ በፊት ጎን ለጎን ሆነው ጠላትን ሲዋጉ የነበሩ ወንድሞች አሁን ደግሞ እርስ በርስ ለመዋጋት መዘጋጀታቸውን ነው የሚያስረዳው። ይሁን እንጂ መሠዊያው የተሠራበትን ትክክለኛ ዓላማ በመረዳታቸው ሳይዋጉ ቀሩ። የዓላማ መግባባት በመኖሩም ሁሉም ደስ አላቸው።

1-3 መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ 22 ካላነበብህ አሁኑኑ አንብበው። በተለይም ከ11-24 ያሉትን ቁጥሮች በጥንቃቄ አንብባቸው። ከዚያም በኋላ እያንዳንዱን ዐረፍተ ነገር የተሟላ የሚያደርገውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

1/ በገሊሎት መሰዊያ መሰራቱን እስራኤላውያን ሲሰሙ፡-

ሀ/ የተሠራበትን ምክንያት አወቁ ሐ/ የተሠራበትን ምክንያት ገመቱ

ለ/ የተሠራበትን ምክንያት ጠየቁ

2/ እስራኤላውያን ተቆጥተው ለውጊያ የተነሱት፡

ሀ/ ሌሎች ነገዶች ኃጢአት በማድረጋቸው

ለ/ ሌሎች ነገዶች ኃጢያት አድርገዋል ብለው ስላሰቡ

ሐ/ ሌሎች የሚያደርጉት ሁሉ ትክክል መስሎ ስለማይታያቸው

3/ የእስራኤል ሕዝብ ተወካይ ወደ ሌሎች ነገዶች ሄደው፡-

ሀ/ ለምን መሰዊያውን እንደሰሩ ጠየቋቸው

ለ/ መሰዊያውን እንዲያፈርሱ ጠየቋቸው

ሐ/ በእግዚአብሔር ላይ አምጻችኋል ብለው ወቀሷቸው።

4/ የተፈጠረውን አለመግባባት ለማስወገድ እስራኤላውያን ምን ማድረግ ነበረባቸው? -------------------------------

5/ የተፈጠረውን አለመግባባት ለማስወገድ የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ምን አደረጉ?--------------------------------------------

ኢያሱን የመሰለ መሪ ያስፈለገበትን ምክንያት ለመገንዘብ ስለሚረዳን ይህ ታሪክ በጣም ጠቃሚ ነው። በዚያን ወቅት ለእያንዳንዱ እርምጃ ግልጽና ጥርት ያለ መመሪያ ማስፈለጉን ጌታ አውቋል። አዲስ ሕይወት እየጀመሩ ስላሉበት ሁኔታ ማወቅ ስለተሳናቸው ከጌታ ዘንድ መልእክት የሚቀበልና ለሕዝቡም መመሪያ የሚሰጥ ጠንካራ መሪ አስፈለጋቸው።

ታላቅ የጦር መሪ እንዲሆን ኢያሱን ያሰለጠነው ሙሴ ነበረ። ከዚህም በበለጠ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃልና ቃሉን መከታተልን ተምሯል። ለመሪነት የጠራውም ራሱ እግዚአብሔር ከመሆኑም ሌላ ***"ለአባቶቻችሁ እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልኩላቸውን ምድር ለዚህ ህዝብ ታወርሳለህና ጽና፣ አይዞህ-----አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና አይዞህ አትፍራ-------"***(ኢያሱ1፣ 6-9) የሚል ተስፋ የተሰጠው ሰው ነበር።

ምናልባትም ኢያሱ ስለራሱ ዝቅተኛ ግምት ያለውና ፈሪ ሳይሆን ስለማይቀር ሊሆን ይችላል እግዚአብሔር እየደጋገመ አይዞህ የሚለው። ስለጥሪው እርግጠኛ ከሆነ በኋላ ግን ድፍረቱንና በራስ መተማመኑን ሲያስመስክር እናገኘዋለን። መሪነቱን የጀመረው፣ ***"አምላካችሁ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ወደሚሰጣችሁ ምድር እስከ ሦስት ቀን ይህን ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ልትወርሷት ትገቡባታላችሁና ስንቃችሁን አዘጋጁ"*** የሚል የማያሻማ ትእዛዝ በመስጠት ነበር። (ኢያሱ 1፣10-11)።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ኢያሱ ግልጽ የሆነ መልእክት ለሕዝቡ ሲያስተላልፍና መልእክቱን ለማስተላለፍ የሚያስችለውን ችሎታ እንዳዳበረ እንገነዘባለን፡፡ በመጽሐፈ ኢያሱ ሰባት መልእክትን ወይም ሀሳብን ለሰዎች ያስተላለፈበትን መንገዶችን እናገኛለን፡፡ እያንዳንዱን በዝርዝር ለመረዳት እንዲረዳህና ለወደፊቱ በቀላሉ ልታገኛቸው እንድትችል ኢያሱ ያስተላለፋቸውን መልእክቶች በመጽሐፍ ቅዱስህ ላይ አስምርባቸው፡፡

*መመሪያ ቃላት*

*መጽሐፈ ኢያሱ* 2፡1፣ 3፡2-4፣ 9፡8፡ 3-8

ባለሥልጣኖቹ ወደ ሰፈር ሄደው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለሕዝቡ ነገሯቸው፡፡ ለጉዟቸውም ሆነ ለሚደርጉት ውጊያ የሚሰጣቸውን መመሪያ ሕዝቡ በትክክል መስማትና መረዳታቸውን ማረጋገጥ የኢያሱ ዓይነተኛ ባሕርይ ነበር፡፡ የሚያስፈልግ ከሆነም መመሪያዎቹን ደግሞ ደጋግም ይነግራቸዋል፡፡ አስፈላጊውን ሥራ ለተለዩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ይሰጣል፡፡ በኃላፊነት ለሚሳተፉትም የሥራ ድርሻቸውን ያብራራላቸዋል፡፡ **"ስሙ፡ አድምጡ"** በማለት የሚሰጣቸውን መመሪያ በትክክል እንዲቀበሉ ያነቃቸዋል (ኢያሱ 3፣9)፡፡ ምንም አድበስብሶ የሚያልፈው ነገር የለም፡፡ የሥራ ድርሻውን እንዲወጣ ለእያንዳንዱ ሰው በቂ መረጃ ይሰጠዋል፡፡

በጥንቃቄ የሚሰጥ መመሪያን ተቀብለው ሰላዮቹ ወደ ረሐብ ሲሄዱ፣ የዮርዳኖስን ወንዝ ሲሻገሩ በኢያሪኮ መውደቅና ዘመቻ ሲያደርጉ በተገኘው ውጤት መመልከት ይቻላል፡፡ በጣም ጥቂት ከሆኑ ሰዎች በስተቀር ሕዝቡ **"ኢያሱ እንዳዘዛቸው አደረጉ"** (ኢያሱ 4፡8፡፡) የሚያደርጉትንና የሚጠበቅባቸውን እንደሚገባ ስለሚያውቁ በፍጹም መተማመንና እርስ በርስ በመተባበር ሥራቸውን አከናወኑ፡፡

**የማበረታቻ ቃል**

*መጽሐፈ ኢያሱ* 3፡5፣ 10፡24-25፣ 23፡5

ኢያሱ ሕዝቡን፡- ***"በቅርቡ በእነዚህ ነገሥታት አንገት ላይ እግራችሁን አኑሩ፣ እግዚአብሔር በምትወጓቸው በጠላቶቻችው ሁሉ ላይ እንዲህ ያደርጋልና አትፍሩ፣ አትደንግጡ፡ ጽኑ አይዞአችሁ"*** አላቸው (ኢያሱ 10፡24-24)፡፡ ድልንም ሆነ ማበረታታትን ከሕዝቡ ጋር በመካፈሉ የሚያገኙት ድል አንድን ሥራ ከማከናወን በላይ መሆኑን እንዲገነዘቡ ይረዳቸው ነበር፡፡ ወደፊት ለሚደረገው ነገርም ተስፋ ስለሚሆን፣ ቀጣይነት ያለው የእግዚአብሔር በረከት ማስረጃ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ሕዝቡ በእምነት እየበረቱ በመሄዳቸው የሚጠበቅባቸውን በፍጹም ልባቸው ለማከናወን በቁ፡፡

**ትእዛዛትና ሥርዓት- መጽሐፈ ኢያሱ 6፡16**

እንደ ጦር መሪነቱ ኢያሱ ለሕዝቡ ቀጥተኛና የማያወላውል ትእዛዝ መስጠት እንዳለበት ተረድቷል፡፡ ኢያሪኮ በወደቀችበት ጊዜ ከሆነው ሁኔታ እንደምንመለከተው አንድ መሪ ከሕዝቡ ፍጹም ታዛዥነትን የሚጠብቅበት ወቅት ይኖራል፡፡ ኢያሱ ለተከታዮቹ የሚያስብና የሚያከብር መሪ ምሳሌ ነው፡፡ በዚያው መጠን ሕዝቡም ይተማመኑበትና ያከብሩትም ጀመር፡፡ ስለዚህም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፍጹም ይታዘዙለታል፡፡ ይህ መሪዎች በተለይም ደግሞ ከወጣቶች ጋር የሚሠሩ መሪዎች ሁሉ ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌ ነው፡፡

**መረጃ (ትምህርት)** - መጽሐፈ ኢያሱ 24-1-13

ኢያሱ ለሕዝቡ ታሪካቸውንና ዓላማቸውን አስገነዘባቸው፡፡ እንደ አንድ አስተዋይ መሪ ሁሉ ለሕዝቡ ተገቢውን መረጃና አስፈላጊውን ነገር ማሳወቅ ለሥራው መቃናት አስተዋጽኦ እንዳለው ያውቃል፡፡ መሠረታዊው እውነትና የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት የጌታን ሥራ ለሚሠሩ ሁሉ በአዲስ መልክ ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡ ኢያሱ የእግዚአብሔርን ቃል ደግሞ ደጋግሞ ይነግራቸው ነበር እንጂ **"ይህንን ድሮም ታውቁታላችሁ"** የማለት ልማድ አልነበረውም፡፡ መልእክትን ወይም ሀሳብን ለሕዝቡ የማስተላለፍ ጉዳይ አንድ ጊዜ ብቻ ተጠናቅቆ የሚያበቃ ጉዳይ አይደለም፡፡ ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው፡፡

**ማግባባት (ምክር) - መጽሐፈ ኢያሱ** 23፡6-16፣ 24፣14-24

ብዙውን ጊዜ በክርስቲያናዊ ሥራ ውስጥ መልእክት ወይም ሃሳብ የሚተላለፈው በምክር ወይም በስብከት መልክ ነው፡፡ ብዙ መሪዎች ሁሉም የሕዝብ ግንኙነት የዚህ ዓይነት እንደሆነ ያስባሉ፡፡ የመሪዎችን ፈቃድ እንዲፈጽሙ አዘውትረው ሰዎችን ይመክራሉ፡፡ ያበረታታሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሰዎችን ከሚገባ በላይ ማነሳሳትና መገፋፋት ውጤት አልባ ይሆናል፡፡ ኢያሱ ሰዎችን ስለማበረታታት መልካም ምሳሌ ይሰጠናል፡፡ ወደፊት ስለሚጠብቃቸው ነገር ለሕዝቡ እንዲናገር የመራው ራሱ ጌታ ነበር፡፡ ከኢያሱ ንግግር አራት ዋና ዋና ፍሬ ሃሳቦችን የምንረዳው ውጤታማ የሕዝብ ግንኙነት በእነዚህ ነጥቦች ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ነው፡፡

**1/ ለአእምሮ የሚስማማ ጥሪ ማቅረብ፣-** ***"ከዚህ በፊት የሆነውን ሁላችሁም ታውቃላችሁ፤፡ ስለዚህም ያንን ያደረገ እግዚአብሔር ወደፊትም እንደሚያደርግ ማመን አይከብዳችሁም"*** (ኢያሱ 23፡14-16)፡፡

2/ ***ማስጠንቀቂያ፡*** ***"እምላካችሁ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ቃል ስታፈርሱ --- በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ ይነድባችኃል"*** (ኢያሱ 23፡23፡16)፡፡

3/ ***ማበረታታት፡*** ***"በጣም በርቱ"*** (ኢያሱ 23፡6)፡፡

4/ ***ምርጫና ውሳኔ እንዲያደርጉ ዕድል መስጠት፡*** ***"የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ"*** (ኢያሱ 24፡15)

በንግግር መልእክትን ወይም ሃሳብን ማስተላለፍ እንደሚቻል ሁሉ በጽሑፍም ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ ኢያሱ ሁኔታዎችን በጽሑፍ ያሰፍርና የእንቅስቃሴውንም ሪፖርት ይቀበል ስለነበር ከአንድ መሪ የሚጠበቀውን አድርጓል፡፡ ምናልባትም መልክ ባለው ሁኔታ በፋይል መያዙ ብዙ መሪዎች ይስማሙበታል፡፡ እግዚአብሔር የመረጣቸው መሪዎች ስለእርሱና ስለሕዝቡ በጽሑፍ ባያስተላልፉልን ኖሮ ምንኛ ብዙ ነገሮች ባመለጡን ነበር፡፡

**በምሳሌ መልእክትን ማስተላለፍ- መጽሐፈ ኢያሱ 4፡1-9**

"የእነዚህ ድንጋዮች ነገር ምንድነው?" መልእክት ማስተላለፍ ሲባል ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ሁኔታ ከአንድ ሰው ወደ ሌላው መልእክትን ማስተላለፍ ወይም ሃሳብን መግለጽ ማለታችን ነው፡፡ ይህም ሊደረግ የሚችለው በንግግር በጽሁፍና ምሳሌያዊ በሆኑ ነገሮች በመጠቀም ጭምር ነው፡፡ ኢያሱ በድንጋይ ክምር ተጠቅሞ አስፈላጊ የሆነ መልእክትን ለሕዝብ አስተላልፏል፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ የምንመለከታቸው እንደ መሰዊያ፣ መዘምራንና ካህናት የሚለብሱዋቸው ልብሶች ተምሳሌታዊ በሆነ ሁኔና መልእክትን የምናስተላልፍባቸው መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መንበርከክ፣ እጆችን ወደ ላይ መዘርጋት፣ ማጨብጨብ ተምሳሌታዊ መልእክቶች ናቸው፡፡ አንድ መልካም መሪ ከአካል እንቅስቃሴውና ገጹ ላይ በሚነበበው ሃሳብ ሰዎች ትርጉሙን መረዳት አለመረዳታቸውን እርግጠኛ ይሆናል፡፡ ስለዚህም በቃል የሚተላለፈውን ያህል በተምሳሌታዊ መንገድ ማስተላለፍም ውጤት አለው ማለት ነው፡፡

6/ በመጽሐፈ ኢያሱ የተመለከትካቸውን ሰባቱን የመልእክት የማስተላለፊያ መንገዶችን ለማስታወስ ሞክር፡፡ ከዚያ በኋላም ቁጥሩን በክፍቱ ስፍራ በመሙላት አብረው የሚሄዱትን አመልክት፡፡

1. መመሪያ 2.ማበረታታት ትእዛዝ 3. ትእዛዝ 4. መረጃ
5. ማግባባት 6. በጽሑፍ ማስፈር 7. ምሳሌዎች

------ሀ/ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፣፡ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን (ኢያሱ 24-15)፡፡

----ለ/ ኢያሱ በድንጋዮቹ ላይ የሙሴን ሕግ ጻፈባቸው(ኢያሱ 8፣32)

---ሐ/ ወደዚህ ቀርባችሁ የአምላካችሁን የእዚአብሔርን ቃል ስሙ አለ (ኢያሱ 3፡9)

---መ/ ከእናንተም ሰው ሁሉ በእሥራኤል ልጆች ነገድ ቁጥር በጫንቃው ላይ አንድ አንድ ድንጋይ ይሸከም (ኢያሱ 4፡5-6)፡፡

-----ሠ/ አትፍሩ፣ አትደንግጡ፣ ጸኑ አይዞአችሁ (ኢያሱ 10-25)

---ረ/ የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" (ኢያሱ 24-2)

----ሰ/ እናንተ ግን እርም ካደረጋችሁት በኋላ እርም ከሆነው ነገር ራሳችሁን ጠብቁ (ኢያሱ 6፡18)፡፡

## የመልእክት ማስተላለፊያ ሂደት

### ዓላማ 2 የመልእክት ማስተላለፊያ ሂደትንና የሚገጥሙ መሰናክሎችን ለመግለጽ

እስከ አሁን ድረስ ለሰዎች መልእክትን ስለማስተላለፍ በርከት ያሉ ምሳሌዎችን ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ ስለ ሂደቱ በመተንተን አስፈላጊውን ግንዛቤ ለማግኘት እንሞክራለን፡፡ ቀደም ሲል የተመለከትናቸውን አንዳንድ ዝርዝሮችን ለማስታወስ ያህል፣ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ልናስተላልፈው የምንፈልገው መልእክት ወይም መልእክቱን ለማስተላለፍ የሚፈልግ ሰው ይኖራል፡፡ ሰውየው አንድ ዓይነት ፍላጎት ወይም ትርጉም ያለው መልእክት ማስተላለፍ ይፈልጋል፡፡ ይህም ሀሳቡን፣ ስሜቱን ወይም ደግሞ አንድ ዐይነት መረጃ የሚገልጥ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መልእክቱ የሚተላላፍለት ተቀባይ ሰው ይኖራል፡፡ መልእክቱ የሚቀበል ሳይሆን የራሱ ስሜትና ግንዛቤ ያለው ነው፣ ምናልባትም በዚህ በሚተላለፍለት መልእክት ላይ የራሱ ተጽዕኖ ይኖራል፡፡ መልእክቱን አስተላላፊው ሰው ሌሎች ሰዎች ሊገባቸው በሚችል ትክክለኛ የሆነ መንገድ ለማግኘት መልእክቱን የማስተላልፊያ ዘዴዎችን መምረጥ አለበት፡፡ መልእክት የምናስተላልፍበት ዋናው ዓላማ ተቀባዩ መልእክቱን በምንፈልገው መንገድ እንዲረዳልን ለማድረግ ነው፡፡

ብዙዎቻችን ይህን ማድረግ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ አንረዳም፡፡ በሚተላለፈው መልእክትና ተቀባዩ መልእክቱን በሚቀበልበት ሁኔታ መካከል አንዳንድ አለመግባባቶች

ሊፈጠሩ ይችላሉ። ከሰዎች ጋር ስለምንግባበት ሂደት ማወቅ እንደሚገባ ለመረዳት እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ መሰናክሎችን በጣም ይጠቅመናል። ከዚያ በኃላ ደግሞ እነዚህን እንቅፋቶች እንዴት ማስወገድ እንደሚቻልና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዴት መልእክታችንን ለሰዎች ማስተላለፍ እንደሚቻል የሚረዱንን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

1/ **ቋንቋ፡-** አንዳንድ ቃላት ከአንድ በላይ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል። አንዳንድ ቃላት ደግሞ ልዩ ትርጉም የሚሰጡባቸው ስፍራ ይኖራል። ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት ልዩ ወይም ምሳሌያዊ የሆነ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው በዮሐ 3፡1-12 ላይ እንደገና መወለድ የሚለውን ቃል ኒቆዲሞስ በምን ዓይነት መንገድ እንደተረዳው አስተውል። (ዮሐ 3፡1-12 አንብብ) መልእክቱን የሚያስተላልፈውም ሆነ መልእክቱን የሚቀበለው ሰው ቃላቱን በተመሳሳይ መንገድ የማይረዱ ከሆነ እንደሚገባ ተላልፏል ለማለት ያዳግታል።

2/ **ምሳሌዎች፡-** ብዙውን ጊዜ መልእክትን የምናስተላልፈው በንግግር በመግለጽ አይደለም። አንዲት ሴት ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላትን አክብሮትና ፍቅር በመመልከት ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት እንደተነሳሳች አንድ መጋቢ መስክሯል።

ይህ ቀና በሆነ መልኩ በምሳሌያዊ ቋንቋ መልእክት የሚተላለፍበት መንገድ ነው። የሰውነት እንቅስቃሴያችን፣ የእጅ አሰናዘራችን፣ በገጻችን የሚነበበው ሁኔታና ድምፃችን ከምንናገረው ጋር የማይጣጣሙ ከሆነ እንቅፋት ተፈጥሯል ማለት ነው። ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚወድ እየተናገረ መጽሐፍ ቅዱሱን ቢወረውረው ወይም ደግሞ በአቧራ እስኪሸፈን ድረስ ችላ ቢለው ምንድነው የሚያስተላልፈው መልእክት? የአክብሮትና የፍቅር ወይስ የንቀትና የጥላቻ?

3/ **ባሕላዊ አመለካከቶች፡-** እያንዳንዱ ሕዝብ፣ ጎሳ፣ ነገድ ወይም ቡድን የራሱ ባሕል አለው። አንዳንድ ጊዜ ባሕላችን ከሌሎች ሁሉ የላቀና ከሌሎች ይልቅ ትክክለኛ እንደሆነ እናስባለን። ለምሳሌ ያህል በአንዳንድ ባሕሎች ሴቶች ከመጨባበጥ ይልቅ ጉንጭና ጉንጫቸውን ያነካካሉ። እንደዚህ ዐይነት ባሕሎችን የማናከብር ከሆነ ትክክለኛ መግባባት ሊኖረን አይችልም፣ እንዲያውም ጸብ ሊፈጠር ይችላል።

4/ **አግባብ የሌለው ጥላቻ፡-** በእግዚአብሔር ፊት ከራሳችን ጋር እኩል እንደ ሆኑ ከማንገምታቸው ሰዎች ጋር መግባባት አዳጋች ነው። ከንቀት የተነሳ አለመግባባት እንደተፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ በርከት ያሉ ምሳሌዎች ይሰጠናል። አይሁዳውያን

ሳምራውያንና ሌሎች አሕዛብን ከእነርሱ ያነሱ አድርገው ይመለከታቸው ስለነበር ሌላው ቀርቶ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል እንኳ እንዳይቀበሉ እንቅፋት ሆኖባቸዋል። እንዲህ ዓይነቱን አግባብ የሌለው ጥላቻ እንዲያስወግድ ለጴጥሮስ በራዕይ የተናገረው በዚህ ምክንያት ነበር (የሐዋ 10)።

5/ **የደረጃ መበላለጥ፡-** አንዳንድ ሰዎች በደረጃቸው ከእነርሱ ከሚያንሱም ሆነ ከሚበልጡ ጋር ግንኙነት መፍጠር ያስቸግራቸዋል። ለምሳሌ ያህል አንድ ገበሬ ከሜካኒክ ይልቅ እንደርሱ ገበሬ ከሆነ ሰው ጋር በሀሳብ መግባባት ይቀለዋል። ለሠራተኞቻቸው ስለ ጌታ መመስከር የሚከብዳቸው ብዙ ሀብታም ክርስቲያኖች አሉ። ለአለቆቻቸው ወይም ለአሰሪዎቻቸው መመስከር የሚከብዳቸውም ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ይህንን በሚመሳሰሉ እንቅፋቶች ምክንያትም ለጌታና ለሰዎች ያለን ፍቅር ውጤት አልባ ይሆናል። አንድ የተዋጣለት መሪ ግን በተለያየ ደረጃ ካሉ ሰዎች ጋር መግባባትና ሃሳቡንም ለማስተላለፍ መቻል አለበት። ለዚህም የመጀመሪያው ደረጃ ችግሩን መረዳትና ከዚያ ትሕትና በተሞላበት መንገድ ለማስወገድ መጣር ነው።

6/ **የዕድሜና የጾታ ልዩነት፡-** ከደረጃ መበላለጥ ጋር በቅርበት የተያያዘው ሌላው እንቅፋት ደግሞ የጾታ ልዩነት ነው። ሽማግሌዎች ከወጣቶች ጋር በሀሳብ መግባባት ያዳግታቸዋል። ትኩረታቸውና ፍላጎታቸው በጣም ይለያያል። ለምሳሌ ያህል አንድ ጊዜ የቡድኑ መሪ በታቀደው ፕሮጀክት ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግቡ ከሆነ በመጋቢው ቤት የራት ግብዣ እንደሚደረግላቸው ተናገረ። ወጣቶቹ የሚፈልጉት ግን በሐይቁ ዳርቻ መንሸራሸርን እንጂ ከመጋቢው ጋር ራት መብላትን አልነበረም። ይህም መሪውን አናደደው። የታቀደው ፕሮጀክትም ውጤታማ ሳይሆን ቀረ።

በዘመናችን በጣም በመስፋፋት ላይ ያለው እንቅስቃሴ የሴቶች እኩልነት ነው። አስተዋይ ክርስቲያን መሪዎች ይህን በቸልታ አይመለክቱትም። በጉዳዩ ያስቡበታል። ይጸልዩበታል፣ የእያንዳንዱን ጾታ ችግር ለመረዳትና መፍትሔም ለመሻት ይሞክራሉ፣ አዳጋች ቢሆንም እንኳ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ሥፍራ ያለው መሆኑን ስለሚያስታውቃቸው በጣም ይጠቅማቸዋል።

7/ የተማርከውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለሌሎች መልእክት ማስተላለፍ ምን ማለት እንደሆነ በራስህ ቃላት ግለጽ።------------

8/ የተማርከውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መልእክት ለሌሎች ለማስተላለፍ እንቅፋት ስለሆኑ ጉዳዮች ስንነጋገር ምን ማለታችን እንደሆነ በራስህ ቃላት ግለጽ።----------

9/ አንድ ዓይነት እንቅፋት በመፈጠሩ ከሰዎች ጋር አለመግባባት ወይም የሀሳብ መተላለፍ ገጥሞህ እንደሆነ የራስህን ልምምድ አስፍር-------------

## የጠለቀ አስተሳሰብ አስፈላጊነት

## ዓላማ 3 ለሰዎች መልእክትን በማስተላለፍ ሂደት የጠለቀ አስተሳሰብን አስፈላጊነት ለመግለጽ

የመልእክቱ ተቀባይ ግንዛቤና አስተሳሰብ በመልእክቱ ትርጉም ላይ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ በሌላ አነጋገር የመልእክቱ ትርጉም የሚወሰነው በተቀባዩ የጠለቀ አስተሳሰብ መሠረት ነው፡፡ ስለዚህ በተገቢው መንገድ መልእክታችንን ማስተላለፍ ከመቻላችን በፊት መልእክቱ የሚተላለፍለት ሰው ስላለው ግንዛቤ አስቀድሞ ማወቅ ይረዳል፡፡

በከፊል ቢሆንም የአንድ ሰው አስተሳሰብና ግንዛቤ የዕድሜ፣ የጾታ፣ የደረጃ መበላለጥና የባሕል የመሳሰሉት ነገሮች ውጤት ናቸው፡፡ ሌሎች ሁለት ዓበይት ጉዳዮች ደግሞ የግለሰቡ ባሕርይና የሕይወት ልምምድ ናቸው፡፡ መልእክት ለሌሎች ስለ ማስተላለፍ ጥናት ያደረጉ ጠበብት አንድ ዓይነት መልእክት እንዴት የተለያየ ግንዛቤ ሊያሳድር እንደሚችል ለመረዳት እንዲያመቻቸው በሰብአዊ ባሕርይ ምድቦች ይጠቀማሉ፡፡ በዚህ መሠረት አራት ዓይነት የሰብአዊ ባሕርይ ምድቦች ሲኖሩ እነርሱም፡-

1/ **የሐሳብ ሰዎች፡-** መሪው ማንኛውንም ነገር ምክንያታዊ በሆነና ሐቅን በተመረኮዘ መንገድ እንዲያብራራላቸው የሚፈልጉ፡፡

2/ **የስሜት ሰዎች፡-** ስሜታቸውን የሚያነሳሳና የሚያነቃቃ ነገር የሚፈልጉ

3/ **የማየት ሰዎች፡-** እንዴት እንደሚሠራ ለማየት ምሳሌዎች የሚፈልጉ

4/ **የተፈጥሮ አስተዋይነት ያላቸው ሰዎች፡-** በፍጥነት ወደ ማጠቃለያ ሃሳብ የሚደርሱና የተሰወሩ ትርጉሞችን የማግኘት ችሎታ ያላቸው፡፡

በቡድኖቻቸው ውስጥ እነዚህ አራት የባሕርይ ዓይነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚገነዘቡ መሪዎች ለሁሉም የሚስማማ የተመጣጠነ መልእክትን ያቀርባሉ፣ እንዳንድ ሰዎች ለምን ከሌሎች ይልቅ መልእክቱን ፈጥነው እንደሚረዱ ወይም እንደሚቀበሉ ይገነዘባሉ፡፡ በትክክለኛው መንገድ ግለሰቦችን ያቀርባሉ፡፡ ውጤት ባለው መንገድ

ሥልጠናና ምሪት ይሰጣሉ፣ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ባህርይ እንዳለው ያውቃሉና ሰዎች መልእክታቸውን በተሳሳተ መንገድ ቢረዳባቸውም እንኳ አይናደዱም።

ሌላው የባሕርይ ዓይነቶችን የምንመድብበት መንገድ ደግሞ ሰዎች በሚያሳዩት በሌሎች የመደገፍና በሌሎች ከመደገፍ ነጻ የመሆንና በራስ የመተማመን ዝንባሌ ነው። በሌሎች መደገፍን የማይፈልጉ በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎች ግን የራሳቸውን ሃሳብ የመግለጽ ዕድል እንዲሰጣቸው የሚፈልጉ ናቸው። መሪው ዝርዝር መመሪያዎችን እንዲሰጣቸው ሳይሆን አጠቃላይ መመሪያ ብቻ እንዲሰጣቸውና የራሳቸውን የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ የሚፈልጉ ናቸው፣ እነዚህ የተለያየ ዓይነት ባሕርይ ያላቸው ሰዎች አንድን መልእክት በእንዴት ያለ ሁኔታ እንደሚረዱት እንዲያውቅ በማድረግ ለመሪው ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጠዋል።

ማንኛውም ግንዛቤና አስተሳሰብ ባለን ልምምድ ላይ የተደገፈ ነው። ማንኛውም ዓይነት መልእክት የማስተላለፊያ መንገድ ልምምድን ለሌሎች በማካፈል ላይ ሊደገፍ የሚችል ነው። እንዲህም ሲባል የሚተላለፈው መልእክት ተቀባይነት የሚኖረው አስተላላፊውም ሆነ ተቀባዩ በጋራ የሚግባቡበት ቋንቋ ሲኖራቸው ነው ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ሰው አንድን ነገር በተለየ ሁኔታ እንዲያይ የሚያደርገው የራሱ ልምምድ ሊኖረው ይችላል።

ይህም በአስከፊ ጦርነት መሳተፍ፣ በአስፈሪ ማዕበል ውስጥ ማለፍ፣ ወይም እንደስራ አይነቱና የጋብቻ ህይወቱ ሊለያይ ይችላል። ስለ ሥፍራ፣ ሰዎችና አንዳንድ አስተሳሰቦች ያለን ትርጉም ካሳለፍነው ልምምድ የተነሳ በአስደናቂ ሁኔታ ሊለወጥ ይችላል። ስለዚህም የሰዎችን ልምምድ በምንረዳበት መጠን በዚያው ልክ ከእነርሱ ጋር ሃሳብ ለሀሳብ መግባባት እንችላለን ማለት ነው። ማንኛውም ግንኙነት ከዚህ የጋራ ተሞክሮ መነሳት አለበት፣ የምናስተላልፈው ማንኛውም መልእክት ከተቀባዩ የሕይወት ልምምድ ወይም ተሞክሮ ጋር መጣጣም ይኖርበታል።

10/ የአንድ የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊ ከሥራው ጋር የተያያዘ ስብሰባ በመምራት ላይ እያለ **"በጣም ትንንሽ ለሆኑ ሕፃናት የተለየ ክፍል ያስፈልገናል። አስፈላጊውን ቁሳቁስ ካሟላን ደግሞ በዚሁ ቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ ክፍል አለ"** በማለት ተናገረ።

አንዲት የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ የሆነች **"እዎን ለሕፃናት የሚሆኑ መጻሕፍትና ለማስተማሪያ የሚረዱ ብዙ ሥዕሎች ያስፈልጉናል"** አለች። የአምስት

ልጆች እናት የሆነች ሌላ አስተማሪ ደግሞ **"ለሕፃናት መቀመጫ የሚሆኑ ምቹ ወንበሮችና ጥቂት አሻንጉሊቶች ያስፈልጉናል"** በማለት ተናገረች። በዚህ ውይይት የተብራሩት የትኞቹ መገለጫዎች ናቸው?

ሀ/ መሪው ሃሳቡን በትክክል አለማስተላለፉ

ለ/ የመጀመሪያዋ አስተማሪ በራስ የመተማመን ባሕርይ ያላት መሆኗ

ሐ/ ልምምድ በግንዛቤና በአስተሳሰብ ላይ ተጽእኖ ያለው መሆኑ

መ/ የልጆች እናት የሆነችው አሳቢ አስተማሪ መሆኗ

11/ ከላይ የጠቀስነውን የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊ ይህን ትምህርት የጀመርንበትን ምሳሌያዊ ገለጻ እንደገና ተመልከት። ባስቀመጥነው ሰብአዊ ባሕርይ ምድብ ውስጥ እንድታስቀምጠው ብትጠየቅ የትኛው ምድብ ውስጥ ታስቀምጠው ነበር?------

በሌሎች የሚደገፍ ወይም በራሱ የሚተማመን ዓይነት ሰው እንደሆነ ብትጠየቅስ ምን ብለህ ትጠራው ነበር?----------------------------

**መልእክትን የማስተላለፊያ እንቅፋቶችን ያስወግዳሉ**

**ዓላማ 4 መሪዎች በራሳቸውና በሚመሯቸው ሰዎች መካከል አርኪ በሆነ መንገድ እንዴት መልእክት ለማስተላለፍ እንደሚችሉ ለመግለጽ**

እስካሁን ድረስ መልእክትን ወይም ሃሳብን ለሰዎች በማስተላለፍ ረገድ መሪዎች የሚፈጽሙትን ስህተት ተመልክተናል። ይህም ስሕተት የሚያስተላልፉትን መልእክት ወይም ሀሳብ ሰዎች ሁሉ ይረዱልናል ብለው ማሰባቸው ነው። በትክክለኛ መንገድ መልእክትን ማስተላለፍ ውስብስብ ጉዳይ ስለሆነ መልእክታችንን አድማጮች ሊረዱልን በሚችሉት መንገድ ማስተላለፍ የሚቻልበት ሁኔታ ላይ በማተኮር እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ተግባራዊ ሊሆን የሚችሉ ሃሳቦችን እናቀርባለን።

1. **ማስተላለፍ የምትፈልገውን መልእክት እወቅ፡-** መልእክቱን አንተ ራስህ እንደሚገባ መረዳትህን አረጋግጥ። ለሌሎች ከማስተላለፍህ በፊት ራስህ ለራስህ ተናገረው ወይም በጽሑፍ ግለጸው። የተድበሰበሰ ሳይሆን ግልጽና ጥርት ያለ ዓላማ ይኑርህ። የሀሳብህን ዝርዝር ዋና ዋና ነጥቦች በማስታወሻ ላይ የማስፈር ልምድ ይኑርህ።

2. **በሚቻልህ መጠን መልእክቱን ስለምታስተላልፍላቸው ሰዎች ዕወቅ፡-** አንድን መልዕክት ወይም ሀሳብ ሁሉም ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ ሊረዱት እንደማይችሉ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ ይሁን እንጂ የሰዎችን ግንዛቤ፣ የስብዕና ዓይነቶችንና የተለያዩ ተሞክሮዎችን እንደሚገባ የሚረዱ መሪዎች መልካም ውጤት ማግኘት ይችላሉ፡፡ ስለሰዎች ብዙ ባወቅህ መጠን፣ በዚያው ልክ ተሞክሯቸውን ትካፈላለህ፣ በዚያው ልክ በአጥጋቢ ሁኔታ መልእክትህን ልታስተላልፍላቸውም ትችላለህ፡፡
3. **ትክክለኛው ግልጽ በሆነ አነጋገር ተጠቀም፡-** ግልጽና ቅንነትን በሚያንጸባርቁ ቃላት እንጂ፣ ወደኋላህ የምትለው ነገር ያለህ ይመስል ንግግርህ ድብስብስ አይሁን፡፡ በሚቻልህ መጠን አፍረጥርጠህ ንገራቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ነገር እንደሚሆን እገምታለሁ በሚሉ ድብስብስ ቃላትን አስወግድ፣ ችግር ካለ ለሁሉም በግልጽ ተናገር እንጂ ስሙን ለመግለጽ የማትፈልገው ሰው አንድ ጥፋት እንዳጠፋ አትናገር፡፡ ሰዎች ላይረዱህና ምናልባትም ሊጎዱ ወይም ሊናደዱ ይችላሉ፡፡
4. **ምላሽ እንዲሰጡ አበረታታቸው፡-** መልእክትህን እንደሚገባ ተረድተው እንደሆነ ከምታረጋግጥበት መንገድ አንዱ እንዲጠይቁና ሀሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ ነው፡፡ ዘወትር መረጃዎችን ስጥ፡፡ ይህንንም ለቡድኑ የሚያስተላልፉ ሰዎችን መምረጥ ትችላለህ፡፡ ማንኛውንም አስተዋፅዖ በአክብሮት እንደምትቀበል በቃልህም ሆነ በድርጊትህ አሳያቸው፡፡

12/ ስለ አፍኬ ታስታውሳለህን? ለትክክለኛ መልእክት ማስተላለፊያ ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች፡-

ሀ/ ማስተላለፍ ስለምትፈልገው መልእክት ደህና ዕውቀት መኖር

ለ/ ግልፅና ጥርት ባለ አነጋገር መጠቀም

ሐ/ ስለምትናገራቸው ሰዎች ማወቅ የሚቻልህን ያህል ማወቅ

## ማድመጥ መልእክትን የማስተላለፍ አንደኛው ክፍል ነው

የተዋጣላቸው መሪዎች መልእክትን የማስተላለፋቸውን ያህል ሌሎችንም ያደምጣሉ፡፡ ማድመጥ አራት ሂደቶችን ያካትታል፡፡ የመጀመሪያው መስማት ነው፡፡ እንዲህም ሲባል የድምጽ ርግብግቢትን መቀበል ማለታችን ነው፣ ሁለተኛው ትኩረት

መስጠት ነው። ብዙ ድምጾችን እንሰማለን፣ የምንሰማቸውን ድምጾች ሁሉ ግን ትኩረት አንሰጣቸውም። ከምንሰማቸው ድምጾች መካከል አንዱን ስንመርጥ ግን ትኩረት ሰጥተነዋል ማለት ነው። ትኩረት ከሰጠነው ደግሞ መልእክቱን ለመረዳት ዝግጅት አድርገናል ማለት ነው። የመጨረሻውና አራተኛው ማስታወስ ነው። መልእክቱን ተቀብለን በአእምሯችን ውስጥ ሰናኖረው ሁሉንም የማድመጥ ሂደቶችን አሟላን ማለት እንችላለን። በትክክል አደመጥህ የሚባለው ሌላው ሰው ለተናገረው ትኩረትህን ስትሰጠው ነው። ይህም ጥረትን ይጠይቃል። ለምሳሌ ያህል አዋቂዎች ሕፃናት ሲናገሩ ይሰማሉ፣ ሆኖም በሚገባ አድምጠውታል ማለት አይደለም። ይህን ያህል ጠቃሚ እንዳልሆነ ስለምናስብ ትኩረት አንሰጠውም። ራስህን የበላይ አድርገህ የምትመለከት ከሆነ የሌላውን ሀሳብ መቀበል ያዳግትሃል። ከቸኮልህ ወይም አእምሮህ በሌላ ጉዳይ ተይዞ ከሆነ ቃላቱን ብቻ ትሰማለህ፣ እንዲያውም እንደሚገባ ሳታደምጥ መልስ መስጠት እንኳ ትችላለህ።

ፍላጎት ካለህ የማድመጥ ችሎታን ማዳበር ይቻላል። "**ይህ ሰው ሊናገር የሚፈልገውን እንደሚገባ ማድመጥ አለብኝ**" በማለት ራስህን ሥርዓት በማስያዝ ሰውየው ሊናገር የሚፈልገው ዋጋ ያለው ነገር ዋጋ ሊኖረው እንደሚችል እመን። እንደሚገባ ማድመጥ የምትፈልግ ከሆነ የሚከተሉትን ተግባር ላይ አውል።

1/ ሃሳብህን በሙሉ በሚናገረው ነገር ላይ አድርግ።

2/ የሚናገረው ነገር እንዳስደሰተህና በንቃት እየተከታተልህ መሆኑን በአካልህና በዓይኖችህ ግለጽ።

3/ በምንም ዓይነት ተናጋሪውን አታቋርጥ።

4/ ተናጋሪው መልእክቱን እስኪጨርስ ድረስ አለመስማማትህን አትግለጽ። ከዚህ ይልቅ ግን ራስህን በማነቃነቅና ወደፊት የምትግባቡበትን ነጥብ አድምጠው።

5/ አጠቃላይ መልእክቱን ተረዳ እንጂ፣ የተወሰኑ ቃላት ላይ አታተኩር።

6/ ትዕግሥተኛ ሁን፣ ችኩልትንና ለሌላ ጉዳይ መጣደፍህን አታሳይ።

7/ ያልተረዳኸው ካለ ጥያቄ አቅርብ፣ ጥያቄህ ረጋ ያለና ዓላማ ያለው ይሁን።

8/ መልእክቱ ካበቃ ባኋላ አስተያየት ስጥ እንጂ በስሜት ተገፋፍተህ አትስጥ።

9/ መልእክቱን ለማመዛዘንና ትክክለኛ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችልህ ከተነገረው ውስጥ ሃቁን ከሃሳቡ ለመለየት ሞክር።

10/ ተናጋሪው ከአንተ ምን ዓይነት ምላሽ እንደሚጠብቅ ጥረት አድርግ ምናልባት ከአንተ የሚፈልገው መረጃ፣ እርዳታ ወይም ደግሞ በሀሳቡ መስማማትህንና ከጎኑ እንደምትቆም ማወቅ ሊሆን ይችላል፡፡

13/ ከቡድኑ አባሎች አንዱ **"ሠይጣን እቅዳችንን አደናቅፎብናል፣ በመሆኑም ስድስት ሰዎች ስብሰባችን ላይ አልተገኙም፡፡ ምን ማድረግ አለብን?"** ሲል ተናገረ፡፡ የቡድኑ መሪ ግን፡- **"ሁሉንም ነገር ሠይጣን ላይ አታሳብብ"** የሚል ምላሽ ነበር የሰጠው፡፡ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማድመጥ መሪው ማሟላት ያቃተው ነገር ምንድነው?"

## የማሻሻያ አስተያየት መቀበል

የተሳካላቸው መሪዎች መልእክት ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ሰምተው እንዴት ማሻሻል እንዳለባቸው የውቃሉ፡1 መልእክት የማስተላለፍ ሂደት ከተናጋሪው ተነስቴ አድማጩ ዘንድ ይደርሳል፡፡ ከዚያም መልእክቱ ይመለስና ተናጋሪውው ዘንድ ይደርሳል፣ ይህ ሂደት የማደርሰው መልእክት በቃል ወየም ስሜትን በመግለጽ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለማድመጥ ስንነጋገር እነደተመለከትነው በትክክል ማድመጠ ምላሽ ወይም አስተያየት መስጠትን ይጠይቃል፡፡

ሰዎች ከመሪው ጋር ሃሳብ ለመለዋወጥ በሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ምላሽ ካላገኙ እንደተናቁ ያስባሉ፣ ወይም መሪውን ይንቃሉ፡፡ ምላሽ የሚሰጥ ከሌለ ሰው በሌለበት በባዶ ክፍል ውሰጥ ተናግሮ እንደመውጣት የሚቆጠር ነው፡1 ይህ ለሰዎች ከመናገር በጣም የራቀ ነው፡፡ ልዩቱ ባዶ ስፍራ ብቻ ሳይሆን ምላሽ የሚሰጥህ ባለመኖሩ ጊዜ በከንቱ መባከኑ ነው፡፡ መሪው መልካም ምላሽ የማይሰጣቸው ከሆነም ሰዎች የማያመች ስሜት ነው የሚሰማቸው፡፡

መልእክት በማስተላለፉ ሂደት አስተያየት መስጠትና መቀበል ተናጋሪውና ሰሚው በትክክል መግባባታቸውን ለመረዳት ያስችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሰዎች ገጽታ ላይ የምንመለከተው መልእክትህን በሚገባ መረዳታቸው ወይም አለመረዳታቸውን ነው፡፡

አስተያየት የመስጠትና የመቀበል ሌላው ጠቀሜታ ደግሞ ስለ ራስህ ያለህን ግምት እንድታዳብር ማድረጉ ነው፡፡ መሪው አስተያየት የሚሰጠው ሰዎችን ለማበረታታትና የታሰበውን ብቃትና ችሎታ እንዲረዱ ለማድረግ ነው፡፡ ስህተታቸውን በማሳየትና በማንጓጠጥ የምንሰጠው አሉታዊ አስተያየት ግን ሰዎችን ተስፋ ሊያስቆርጣቸውና ራሳቸውን ብቃት እንደሌላቸው አድርገው እንዲያስቡ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

የምንሰጠው አስተያየት በከፍተኛ ደረጃ የሥራ እንቅስቃሴው ላይ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል። ከመሪዎቻቸው የሚፈልጉትን አስተያየት የማያገኙ ሰዎች ሥራቸውን በሚገባ ለመወጣት እንደሚያዳግታቸው በዚህ ላይ በማተኮር የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ። መልካም የሥራ እንቅስቃሴ በከፊልም ቢሆን በራስ የመተማመን ውጤት ነው። ከዚህም በላይ እያንዳንዱ ሠራተኛ ሥራውን በሚገባ መረዳቱን መገንዘብ ለመሪው ልብ እረፍት ይሰጣል። አብዛኛውን ጊዜ አስተያየት የምንሰጠው ቢሆንም፣ የተዋጣላቸው መሪዎች ግን ፍሬያማና ውጤታማ የሆነ አስተያየት የሚሰጡት በሚገባ ተረድተውና ሆን ብለው ነው። በመንፈሳዊ አገልግሎት ሰዎችን ስትመራ የምትሰጠው አስተያየት የተሠራውን ሥራ በመገምገም ለተሻለ ውጤታማነት እገዛ ለማድረግ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል የመምህራንን ቡድን እየመራህ ከሆነ የማስተማር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ልትረዳቸው ትወዳለህ። በቡድንም ሆነ በግለሰብ ደረጃ በሚኖርህ ውይይት የተገኘውን ውጤት ወይም ለእነርሱ ያለህን አመለካከት ለመሰንዘር እድል ታገኛለህ። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አስተያየት ለመስጠት የሚረዱህን ነጥቦች በማጥናት በሥራ ላይ ለማዋል ሞክር።

1/ **ግምት የምትሰጠው ለሥራው እንጂ ለግለሰብ አይሁን።** ለሥራው ቸልተኛ ነው ወይም ለእግዚአብሔር ሥራ ግዴለሽ ነው የሚለውን ሃሳብ ሳትሰነዝር፡- "**ይህ ሥራ መሻሻልና በሚገባ መሠራት አለበት**" በል፣

2/ **ገምጋሚ ከሆኑ ቃላት ይልቅ ገላጭ በሆኑ ቃላት ተጠቀም።** አንድን አስተማሪ ሰነፍ ነህ ከማለት ይልቅ በቂ ጥናት ወይም ዝግጅት ማድረግ አለብህ ማለት ይሻላል፣

3/ **አስተያየት የምትሰጥበት ጊዜ ወሳኝነት አለው፡-** አንድ ሠራተኛ እገዛ ወይም ምክር ሲጠይቅህ የሚቻል ከሆነ ወዲያውኑ ምላሽ ስጠው፣ ሰዎች ተስፋ በቆረጡበት ሁኔታ ወይም ደግሞ በቂ የውይይት ጊዜ ሳይኖር እርማት መስጠት አይቻልም።

4/ **የምትሰጠው ምላሽ መጠን በጣም አስፈላጊ ነው፡-** ብዙውን ጊዜ እንደሚታየው በጣም የተመጠነ አስተያየት መስጠት ይሻላል። በሌላ በኩል ደግሞ መሪው ሰዎች እርግጠኛነት እንዳይሰማቸው ማድረግ የለበትም።

14/ ለሰዎች መልእክት የማስተላለፍን ሂደት በአጭሩ ግለጽ።------------------

15/ መልእክትን ወይም ሃሳብን በማስተላለፍ ረገድ የመሪዎች ዋና ዋና ኃላፊነቶች ምንድናቸው?-------------------------------------------------------

**የሙከራ ፈተና**

እንደ እስራኤል መሪነቱ ኢያሱ ጠቃሚ የመሪነት መመሪያዎችን አሳይቷል። ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው ካሳያቸው መመሪያዎችን ጋር አብሮ የማይሄደው?
ሀ/ ኃላፊነትን ለሚጋሩት ሁሉ ስለሥራው መመሪያና ገለጻ ይሰጥ ነበር።
ለ/ የሚሰጣቸውን መመሪያ በትክክል እንዲፈጽሙ ይነግራቸዋል።
ሐ/ ያለፈውን ትውልድ ችግር እያነሳ እነርሱንም የሚጠብቃቸው ያው እንደሆነ ይነግራቸዋል።
መ/ የሕዝቡን እምነት ያበረታታና ያሳድግ ነበር።
2/ እስራኤል የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ ማወቅ አለባቸው። መረጃ ያስፈልጋቸዋል። ይህንንም እንዳይዘነጉት ኢያሱ በሚያሳምን አነጋገር መንፈሳዊ ግዴታዎቻቸውን ነግሯቸዋል። ይህ ለረጅም ጊዜ የሚተላለፍ መረጃ፡-
ሀ/ ሲወርድ ሲዋረድ በሚተላለፍ መልኩ መልእክትን በቃላት መግለጽ
ለ/ ሀይማኖታዊ ሥርአቶችን የሚፈጽሙና ለሕዝቡ የሚያብራሩ ካህናትን ማደራጀት ነው።
ሐ/ ላለፈው ዋጋ የሚሰጥ ባሕልን ማዳበር።
መ/ የመንፈሳዊ ሕይወት ኃላፊነቶችንና መብቶችን ለሌሎች የሚያስተላልፉ መዝገቦች።
3/ ጃስፐር በሰዎች ወደተሞላ ቤተክርስቲያን ገባ። አምልኮው ምሥጋናው፣ የቃሉ አገልግሎትና ሌላው ቀርቶ መሠዊያውና በቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ቁሳቁሶች እንኳ ሳይቀሩ የተለየ ስሜት አሳድረውበታል። ይህም ስሜቱ የምን ውጤት ነበር?

ሀ/ ተምሳሌታዊ በሆነ ሁኔታ መልዕክትን ማስተላለፍ
ለ/ ጽኑ እምነት ስለነበረው
ሐ/ ለሀይማኖታዊ ልምዶች ከሚገባ በላይ ንቁ በመሆኑ
መ/ ለመንፈሳዊ ነገሮች ልዩ ግምት በሚሰጥ ባህል ውስጥ በማደጉ
4/ መልዕክት ለሌሎች ሰዎች የማስተላለፍ ሂደት አላማው የመልእክቱ ተቀባይ
ሀ/ የሚተላለፈውን መልእክት እንደሚገባ እንዲሰማ ማድረግ ነው ለ/ የመልእክቱ አስተላላፊ እንዳቀረበው ትርጉም እንዲረዳ ማድረግ ነው
ሐ/ መረዳት በሚገባው መንገድ የተነገረውን መልእክቱን መረዳት ነው
መ/ ተናጋሪውም ሆነ አድማጩ ተመሳሳይ ግንዛቤ አላቸው።
5/ ትክክለኛ የሃሳብ መግባባት ተፈጥሯል ማለት የሚቻለው፡-

ሀ/ ተናጋሪውና ሰሚው በአንድ ዓይነት ሁኔታ እውነቱን መገንዘብ ሲችሉ

ለ/ ለሕይወት ተመሳሳይ ግንዛቤ ሲኖራቸውና የሚወድዱትም ሆነ የሚጠሉት ተመሳሳይ ሲሆን፡፡

ሐ/ ቃላትን በተመሳሳይ መንገድ መረዳት ሲችሉ፡፡

መ/ ለምሳሌያዊ አነጋገሮች አንድ ዓይነት ግንዛቤና መረዳት ሲኖራቸው፡፡

6/ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪው አገር ሰዎች ሰላምታ የሚሰጣጡት ጉንጭ ለጉንጭ በመሳሳም ነው፡፡ ከውጭ አገር ከተመለሰ ወዲህ ግን አስተማሪው ይህን ልማድ ችላ በማለቱ ሰዎች ቅር ተሰኝተዋል፡፡ ባሕሉን ባለመጠበቁና በዚህም ምክንያት ሰዎች ቅር ስለተሰኙበት ምንድነው ማለት የሚቻለው?

ሀ/ የአገሩ ሰዎች አግባብ የሌለው ጥላቻ አላቸው

ለ/ የሰንበት ትምህርት ቤቱ አስተማሪ ከፍተኛ በደል ፈጽሟል

ሐ/ አስተማሪውና ጓደኞቹ የባህልን ጉዳይ መመርመር አለባቸው

መ/ መልዕክት ማስተላለፊያው መንገድ ተቋርጧል

7/ መልእክት ማስተላለፍ ሂደት የመጨረሻ ውጤት፡-

ሀ/ የመልዕክቱ አስተላላፊ ያሰበውን ትርጉም መያዝ

ለ/ ማንኛውን አድሎ የሌለው ምስክር ትርጉሙን ማግኘት

ሐ/ የመልእክቱ ተቀባይ ትርጉሙ ሲገባው

መ/ ትርጉሙን በቃላቶቹ ትርጉም በግልጽ ሲያመለክት፡፡

8/ መልእክታቸውን ሲያስተላልፉ መሪዎችን የሚፈጽሙት ትልቅ ስሕተት፡-

ሀ/ ሰዎች ሁሉ መልእክታችንን ሊረዱልን ይችላሉ ብለው ማሰባቸው

ለ/ የሚናገሩትን ሁሉ አድማጮች ይረዱታል ብለው ማሰባቸው

ሐ/ በመሪዎችና በተከታዮቻቸው መካከል ያለው ስፍራ በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ግንኙነት ማድረግ ይቻላል ብለው ማሰባቸው

መ/ አብዛኞቹ ሰዎች መልእክታችንን ይረዱልናል ብለው ማሰባቸው

9/ መልእክት በመቀበልና በማስተላልፍ ውስጥ ማድመጥ ከፍተኛ ሥፍራ ስላለው እንደሚገባ አደመጥን ማለት የምንችለው፡-

ሀ/መልእክቱን ስንሰማ ለ/ ለመልእክቱ ሙሉ ትኩረታችንን ስንሰጠው

ሐ/ ስንሰማ፣ ትኩረታችንን ስንሰጠውና መልእክቱን ስንረዳ

መ/ መልእክቱን ተረድተን በአእምሯችን ውስጥ ስናኖረው

10/ አንድ መልእክት ተገቢ ምላሽ አግኝቷል የሚባለው መልእክቱ ከተቀባዩ ተነስቶ ወደ ተናጋሪው ሲመለስ ነው፡፡ ከሚከተሉት ውስጥ አስተያየት መስጠት ከአንዱ በቀር በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ከእነዚህ አንዱ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ አስተያየት ተናጋሪውና ሰሚው በትክክል እንዲግባቡ ያደርጋል

ለ/ አስተያየት ሰዎች ስለ ራሳቸው ያላቸውን ግንዛቤ የሚያዳብሩበት ነው

ሐ/ አስተያየት መሪው መመሪያዎችን ለማውጣት የሕዝቡን ስሜት እንዲገመግም ያስችለዋል፡፡

መ/ አስተያየት ሠራኞቹ ለሥራው በሚያደርጉት አስተዋፅኦ ላይ ከፍተኛ ውጤት አለው፡፡

11/ የሚከተሉትን የመልእክት ማስተላለፊያ እንቅፋቶች ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በመጻፍ ከትክክለኛ ገለጻቸው ጋር አዛምድ፡- 1/ ቋንቋ 2/ ምሳሌ

3/ ባሕል 4/ ንቀት 5/ የደረጃ መበላጥ 6/ እድሜና ጾታ

7/ ሰብአዊ ባሕርይ

------ ሀ/ አንድን ሰው ከሌሎች የሚለየው

-----ለ/ አንድን ትውልድ ከሌሎች የሚለያቸውና የወንዶችንና የሴቶችን ባሕርይ የሚገልጸው

-------ሐ/ ትርጉም የሚሰጥ የቃላት ቅንጅት

------መ/ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል መሆናቸውን

-------ሠ/ የደረጃ መበላለጥ አለመቀበል

-------ረ/ አንድን ሰው ከእርሱ ካነሱት ወይም ከበለጡት ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዳይኖረው የሚያደርግ

-----ሰ/ ያለምንም ቋንቋ መልእክትን ማስተላለፍ የሚቻልበት መንገድ

12/ የተሳካ የመልእክት ማስተላለፍና መቀበል እንዲኖር የሚረዱ ሀሳቦችን ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በማስቀመጥ ከትክክለኛው ገለጻ ጋር አዛምድ፡፡

1/ የምትናገረውን ማወቅ 2/ አድማጮችህን ማወቅ 3/ አድማጮችህን ማክበር

4/ ትክክል፣ ግልጽ በሆነ ቋንቋ መጠቀም 5/ ሰዎች አስተያየት እንዲሰጡ ማበረታተት

-------ሀ/ የሰዎችን ግንዛቤ የሰብአዊ ባሕርያቸውንና ልምምዳቸውን አስቀድሞ ለማወቅ ወስን፡፡

------ለ/ የተድበሰበሱ ቃላትን በማስወገድ ግልጽነት ባለቸው ቃላት ተጠቀም

-----ሐ/ ጥያቄ እንዲያቀርቡና ሃሳብ እንዲሰጡ በማድረግ ሃሳባቸውን ተቀበል

-----መ/ ለሰዎች፣ ለችሎታቸውና ለስጦታዎቻቸው እንዲሁም ለስሜቶቻቸው በእኩልነት አድናቆት ይኑርህ፡፡

-------ሠ/ ማስተላለፍ የምትፈልገውን መልእክት እንደሚገባ አጥንተኸው እንደሆነ ለማወቅ እንዲረዳህ በማስታወሻህ ላይ በቅደም ተከተል ያሰፈርካቸውን በመጠቀም ልምምድ አድርግ፡፡

መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" በመጻፍ መልሰ ስጥ

------13/ መሪው የተለያዩ የሰብአዊ ባሕርይ ዐይነቶችን መረዳቱ የተመጣጠነ መልእክቱን እንዲያቀርብ ከማስቻሉም በላይ ከሰዎች ጋር በተሻለ ሁኔታ እንዲያቀርብ ይረዳዋል፡፡

---- 14/ በሌሎች የሚደገፍ ሰው ከበላዩ ካሉት ሰዎች ዝርዝር መመሪያ ይፈልጋል፣፡ ከሌሎች ይልቅ ትኩረት ይሻል፡፡

እንዲጫኑት አይፈልግም፣፡ ስለ ሥራውም

ዝርዝር መመሪያ እንዲሰጠው አይፈልግም፡፡

------- 16/ መልእክት አስተላላፊውና ተቀባዩ የጋራ የሆነ ልምምደ ካላቸው በመካከላቸው ተገቢ ግንኙነት እንዲኖር ሁኔታዎች ሁሉ ተሟልተዋል ማለት ነው፡፡

-----7/ በአንድ ማሕበረሰብ የሚኖሩ ሰዎች በአንድ ዓይነት መንገድ እንዲያስቡ የሚያደርጓቸው ተመሳሳይ ልምምድ አላቸው፡፡

**የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች**

8/ የሕዝብ ግንኙነት እንቅፋቶች ስንል የተናጋሪው በሚፈልገው መንገድ የመልእክቱ ትርጉም ወደ ሰሚው እንዳይደርስ የሚያደርግ ማንኛውንም መሰናክል ማለታችን ነው፡፡

1/ሐ/ ምን እንደተሰራ አስቡ

9/ መልሶችህ 2/ለ/ ሌሎች ነገዶች ኃጢአት ሰርተዋል ብለው አሰቡ

10/ ሐ/ የሕይወት ተሞክሮ በግንዛቤ ላይ ጫና አለው

3/ ሐ/ በእግዚአብሔር ላይ እንዳመጹ አሰቡ

11/ ንቁ:- ይህም ማለት ቶሎ ብሎ ወደማጠቃለያው ሃሳብ የሚደርስና ስውር መልእክቶችን የሚረዳ ሰው ማለት ነው በራሱ የሚተማመን፡፡

4/ ኃጢአት አድርገዋል ብለው ከማሰባቸውና ለጦርነት ከመዘጋጀታቸው በፊት ለምን ያንን መሰዊያ እንደሰሩ ሌሎች ነገዶችን ሊጠይቋቸው ይገባ ነበር፡፡

12/ ሐ/ በተቻለህ መልእክቱን ስለምታስተላልፍላቸው ሰዎች እወቅ፡፡

5/ ምን እያደረጉ እንደሆነ ለመግለጽ ለእስራኤላውያን መልእክተኞችን ሊልኩባቸው ይችሉ ነበር፡፡

13/ አምስተኛውን ሕግ አላሟላም፣ ማለትም በተወሰኑ ቃላት ላይ ከማተኮር ይልቅ አጠቃላይ ትርጉሙ ላይ ማተኮር ይገባው ነበር፡፡

6/ሀ/5/ ማበረታታት ለ.6/ በጽሑፍ ማስፈር ሐ1/መመሪያ መ.7/ምሳሌያዊ ቋንቋ ሠ/2/ማበረታታት ረ.4/መረጃ መስጠት ሰ.3/ትእዛዝ መስጠት

14/የሰጠኸው መልስ ከእኔ መልስ ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል፣፡ መልእክት ሰሚው ተቀባዩ ሊቀበለውና ሊረዳው የሚችለውን መልእክት ያስተላልፋል፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ተቀባዩ ለመልእክት ሰጪው መልእክት ያስተላልፋል፡፣ ይህም ምላሽ ወይም አስተያየት ይባላል፡፡

7/ መልስህ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የተላለፈ መልእክት ትርጉም ማግኘት ማለት ነው፡፡

15/ መሪው፡፡ 1/መልእክት ግልጽ ለማድረግ 2/ መልእክቱን በትክክል መረዳታቸውን እርግጠኛ መሆን 3/ ምላሽ ወይም አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡